

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድን

የ 2015 ትምትርት ዘመን መሪ እቅድ

መስከረም/ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ክፍል አንድ፡- አጠቃሎ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድን በስሩ የአጠቃላይ ትምህርት የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚሰጡ የቅድመ 1 ኛ እና 1 ኛ ደረጃ እንዲሁም የ 2 ኛ ደረጃ ሱፐርቪዥን ክላስተሮችን በመምራት ሙያዊና አስተዳደራዊ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚሰጥ ቡድን ነው። በ 2014 ትምህርት ዘመን ቡድኑ እና ክላስተሮቹ ተባብሮ በመስራት ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

ከነዚህም ውጤቶች መካከል የሱፐርቪዥን ሽፋኑ በእጅጉ አድጓል ለምሳሌ በአመቱ ከ 27,686 ክፍለ ጊዜ በላይ ክሊኒካል ሱፐርቪዥን መካሄድ ችሏል። ይህ የሚያሳየን ካሉን 110 ክላስተሮች በአማካይ ከ 251 በላይ ክፍለ ጊዜ የሽፈነ ድጋፍ ለመምህራን መስጠት መቻሉን ያመላክታል በተጨማሪም የትምህርት ቤት አመራሩን በቅርበት አስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን በመስጠት በርካታ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ተደርጓል። በመሆኑም የአመቱ የ 8 ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ውጤት 50 ፐርሰንትና በላይ ያመቱ ተማሪዎች ብዛት ካለፉት አመታት በተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱ አንዱ የሱፐርቪዥን ጥብቅ ክትትሉ ውጤት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ይሁንና እነዚህ አበረታች ጥረቶችና ውጤቶች ቢኖሩም ወደ ፊት ከሚጠበቅብን አንፃር ሲታይ ግን ገና ብዙ መስራት የሚጠይቀን መሆኑን በማመንና ጥንካሬና ድክመቶችን በመተንተን የተመዘገበውን አበረታች ውጤት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና የታዩ መልካም ተግባራትን በማስቀጠል በድክመት የተለዩትን ጉዳዮች በማረም ዘጠኝ ክፍል ያለው የ 2015 ትምህርት ዘመን መሪ እቅድን በመተግበር በ 2015 ትምህርት ዘመን ውጤታማ ስራ ለማከናወን የሚያስችል እቅድ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። በውስጡም 4 የትኩረት መስክ እና 10 ዋና ዋና ግቦች አሉት

እነሱም፡- የትኩረት መስክ 1፡-ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት፣ 2፡- ጥራትና ተገቢነት ያለው መማር ማስተማር፣ 3፡- የትምህርት ውስጣዊ ብቃት፣ እና 4፡- የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ዘላቂ እድገት አመራርና አስተዳደር ሲሆኑ ግቦቹ በትኩረት መስክ 1 ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ግቦች ግብ 1. ፍትሃዊ የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ግብ 2፡- ልዩ ፍላጎት ላላቸው እና ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ልዩ ድጋፍ በመስጠት ተሳትፏቸውን ማሻሻል፣ በትኩረት መስክ 2 ጥራትና ተገቢነት ያለው መማር ማስተማር ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ግቦች ግብ 3፡- የትምህርት ጥራት ማሻሻል፡- ግብ 4፡- የመማር ማስተማር ሂደትን መሻሻል ግብ 5፡- ተገቢነት ያለው የስርአተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራን ማሻሻል በትኩረት መስክ 3 የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ማሳደግ ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ግቦች ግብ 6፡- የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ማጎልበት፤ በትኩረት መስክ 4 የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ዘላቂ እድገት አመራርና አስተዳደር ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ግቦች ግብ 7፡- ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ማሳደግ፣ ግብ 8፡- ውጤታማ የሃብት አጠቃቀምን መሻሻል፣ ግብ 9፡- የትምህርት ልማት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አፈፃፀም ማሳደግ፣ ግብ 10፡- የመምህራን፤ የትምህርት አመራሩንና ባለሙያዎችን የመፈፀም አቅም ማሳደግ ናቸው በዚህ ውስጥ አላማዎችና የሚከናወኑ ተግባራት ተካተውበታል። በመቀጠልም ቁልፍና አበይት የድርጊት መርሃግብሮች በዝርዝር ቀርበዋል።

ክፍል ሁለት

2. አጠቃላይ ሁኔታ

መግቢያ

ትምህርት ሰዎች ለመኖር የሚያስችሏቸውን አጠቃላይ ሁኔታዎች ለማሟላት ከተፈጥሮ ጋር እየታገሉ ያከማቹትን ዕውቀት፣ ጥበብ፣ የአሰራር ዘይና የመረጃ አያያዝ እንዲሁም የአለም ሕብረተሰብ በየወቅቱ የደረሰባቸውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ለመጠቀምና ለመጭው /ለተተኪው/ ትውልድ የማስተላለፊያ፣ ብሎም የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የባሕልና አጠቃላይ የአኗኗር ሁኔታ በተሻለ ለማሳደግና ለመለወጥ የሚያስችል ዋነኛ መሣሪያ ነው።

ማንኛውም ሃገር በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማሕበራዊ ኑሮና በባሕል የበለፀገ የሚሆነው ትምህርትን በስፋትና በጥራት በማዳረስ ሕብረተሰቡ ዘመናዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ተፈጥሮን በመለወጥ /በመግራት/ ለእድገት ማዋል ሲችል ነው።

የታለሙ የትምህርት ግቦች ከግብ ለማድረስ፣ ትምህርትን በጥራት ለማዳረስና ውጤታማ ለማድረግ የትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ስራ አንዱ የትምህርት አመራር ስራ ነው። ይህንን እውነታ ወደ ተግባር ለመለወጥ ይቻል ዘንድ በ 2014 ዓ.ም በየደረጃው አቅደን በርካታ ውጤታማ ስራዎችን አከናውነናል በክንውኑም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። በመሆኑም በዚህ አመት ያላሳካናቸውንና ተጨማሪ ማከናወን ያስብንን ተግባራት ከቢሮው እቅድ በመነሳት የቡድኑ የ 2015 ዓ.ም የስራ እቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

የዕቅዱ አስፈላጊነት፡-

በ 2015 በጀት ዓመት የሚፈጸሙ የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቁልፍና አበይት ተግባራትን ለይቶ በእቅድ መመራት እንዲቻል፤ የወረዳ እና ክ/ከተማ ክላስተር ሱፐርቫይዘሮችን ስራ በተቀራረበ አቅም መፈፀም እንዲቻል፤ ክንውኑንም ለመለካት አስፈላጊ ስለሚሆን ነው።

የእቅዱ አጠቃላይ ዓላማ፡-

በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድን በቢፒአር እና በቢሮው የተሰጡትን የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ተግባራትን ውጤታማነት ለማሳደግ ነው።

የእቅዱ ዝርዝር አላማ፡-

የትምህርት ቤት የውስጥ የመምህራንና አመራሩ የርስበርስ ሱፐርቪዥን ሽፋንና ውጤታማነት እንዲሻሻል፤ በወረዳ ወይም በክ/ከተማ ሱፐርቫይዘሮች የሚከናወን ክሊኒካል የውጪ የመምህራን ሱፐርቪዥን ሽፋንና ውጤታማነት እንዲጠናከር፣ የክ/ከተማ፣ ወረዳ እና ትምህርት ቤት አስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን ድጋፍ ክትትል እና ግብረመልስ ሽፋንና ውጤታማነት እንዲጠናከር ማድረግ ነው።

ለትምህርት ልማት ፕላኑ ዝግጅት መነሻነት የተጠቀምንባቸው ሰነዶች፡-

የ 2015 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድን እቅድን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ሰነዶች እንደ መነሻነት ተጠቅመናል፤-

የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድን በቢፒአር የተሰጡት ዋና ዋና ተግባራት፤

የ 2014 በጀት ዓመት የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ቡድኑ አፈፃፀም ሪፖርት፤

የትምህርት ቤት መሻሻልና ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬት የ 2015 በጀት ዓመት መሪ እቅድ

የሰነዱ ዝግጅት ሂደት፣ ሰነዱ የያዛቸውን ክፍሎች/ይዘቶች፤ አደረጃጀት፡-

ይህ እቅድ ዘጠኝ ክፍሎችን የያዘ ሲሆን ክፍል አንድ አጠቃሎ፣ ክፍል ሁለት መግቢያ፣ ክፍል ሶስት የሴክተሩ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴትች፣ ክፍል አራት ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ፣ ክፍል አምስት የቡድኑ ቁልፍ ችግሮች ትንተናና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎች፣ ክፍል ስድስት ዓላማዎች፤ ግቦችና ተግባራት፤ ድርጊት መርሀ-ግብር፤ የማስፈጸሚያ በጀት እና ታሳቢዎች፣ ክፍል ሰባት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና የመፍትሄ አቅጣጫዎች፣ ክፍል ስምንት የክትትልና ግምገማ አግባብ በመጨረሻም ክፍል ዘጠኝ ማጠቃለያ እንዲይዝ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

ክፍል ሶስት፡-

3. የትምህርት ሴክተሩ ተልዕኮ፣ ራዕይና፣ ዕሴቶች፡-

3.1 ተልዕኮ

የትምህርት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ፤ የትምህርት ተቋማትን በፍትሃዊነት በማዳረስና ተገቢ ድጋፍና ክትትል በማድረግ፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ ብቃትና ጥራቱ የተረጋገጠ አጠቃላይ ትምህርት በተስማሚ ፕሮግራሞች ለከተማዋ ነዋሪ መስጠት።

3.2 ራዕይ

በ 2022 ውጤታማ የትምህርት ስርአት በማስፈን አለምአቀፍ ተወዳዳሪና ለሃገር ግንባታ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ትውልድ ማፍራት።

3.3 እሴቶች

- ለለውጥ ዝግጁ ነን፣
- ለትምህርት ጥራት ቅድሚያ እንሰጣለን፣
- ጥናትና ምርምር የችግሮቻችን መፍቻ ነው፣
- በእውቀትና በእምነት እንመራለን/እንሠራለን፣
- በግልጽነት እናገለግላለን፣
- የተጠያቂነት ስርዓትን እናሰፍናለን፣
- ለላቀ አገልግሎት እንተጋለን፣ እንሰጣለን
- በጋራ መስራት መገለጫችን ነው፣
- መልካም ሥነ-ምግባር የዜጎቻችን መለያ ነው፣

3.4 የትምህርት ቢሮ ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

- የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ እንዲቻል ትምህርት ቤቶችን ያስፋፋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲጠገኑ እና መሰረተ ልማታቸው በአግባቡ እንዲሟላ ያደርጋል፤
- የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ደረጃ በመጠበቅ የከተማውን አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ መደበኛ ያልሆኑ፣ ቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፤ መጻህፍት ያሳትማል፤ የትምህርት ግብዓት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ደረጃ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን የአቅም ግንባታ ስራ ያከናውናል፤
- በከተማው ውስጥ አገር አቀፍ ፈተናዎችን ያስፈፅማል፤ በከተማው ውስጥ በሚገኙ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚሠጡ ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ህጋዊነት ያረጋግጣል፤
- ከተማ አቀፍ የሆኑ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፤
- በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ መደበኛና ኢመደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
- ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለጎልማሶችና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ የብቃት መመዘኛዎች መሠረት መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤ ሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት ለሚፈልጉ አካላት የመረጃ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፤
- በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች የመማርና ማስተማር ሂደት በበላይነት ይመራል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

ክፍል አራት፡-

4. ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

4.1 የ 2014 ትምህርት ዘመን አፈፃፀም ግምገማ

4.1.1 የ 2014 ትምህርት አጀማመር ነባራዊ ሁኔታ

የ 2014 ዓ.ም የመማር ማስተማር ሂደትን በወቅቱ ከማስጀመር አንፃር ተግዳሮት ሆኖ የነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ችግር ለመፍታት የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ ጥናቶችን በማድረግ፣ ስትራቴጂ በመንደፍ እና መሰረታዊ የኮቪድ-19 መከላከያ ቁሳቁሶችን በማሟት ችግሩን አስቀድሞ ለመከላከል የተደረገው ጥረት አይነተኛ ሚና ነበረው። ይህንንም መሰረት በማድረግ ትምህርት ከጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ.ም እንዲጀምር ተደርጓል። ከዚህም ሌላ አዋኪ ጉዳዮችን ከትምህርት ቤቶች በማስወገድ ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ ለመፍጠር የተደረገው ጥረት የሚበረታታ ነበር።

የ 2014 ዓ.ም የትምህርት ስራን ውጤታማ ለማድረግ ቀድመን የምንዘጋጅባቸው ስራዎች ወሳኝ ነበሩ። በኮቪድ-19 ምክንያት የ 2013 የማጠቃለያ ምእራፍ ፕሮግራም ለ 2014 ቅድመ ዝግጅት የሚሰራበትን ጊዜ አሳጥሮት ስለነበር ባለው ቀሪ ጊዜ ውስጥ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ለማከናወን በትምህርት ቤቶች የሚታዩ ክፍተቶችን ዳሰሳ ለማኬድ የተሰራው ቼክሊስትና ከቢሮ እስከ ወረዳ ካሉት መዋቅሮች ተውጣጡ ቡድኖች ለተከታታይ 8 ቀናት ያከናወኑት ክትትልና ግብረ-መልስ ለዋናው መማር ማስተማር ስራ ወሳኝ ነበር።

4.1.2 የመማር ማስተማር ክትትልና ድጋፍ ነባራዊ ሁኔታ

የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ስራዎቻችን ውጤት የመማር ማስተማሩን ሂደት በማሳለጥ የተማሪዎችን አካዳሚክ ውጤት፣ ስነ-ምግባርና የትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሳደግ ነው።

በመሆኑም የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያተኩርባቸው ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም ባብዛኛው የሚበረታቱ ቢሆኑም ቀላል የማይባሉ የመማር ማስተማር ስራዎችም አፈፃፀም ድክመት ያላቸው በመሆኑ በሱፐርቪዥን ክትትል ተደርጎባቸው እንዲስተካከሉ ግብአቶች ተሰጥተውባቸዋል።

ከነዚህም ግብረመልሶች ውስጥ መምህራን በግል ወይም በዲፓርትመንት እለታዊ የማስተማሪያ እቅድ አዘጋጅተው መማር ማስተማሩን በውጤት ማካሄድ ላይ ባለን ወቅታዊ መረጃ 95 ፐርሰንት የሚሆኑት መምህራን እቅዳቸውን አዘጋጅተው መስራታቸው በጥንካሬ የሚታይ ሲሆን የቀሩት 5 ፐርሰንት የሚሆኑ መምህራን እቅድ ቢያዘጋጁም ወደ ክፍል ይዞ ባለመግባት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ባለማዘጋጀት ታይተው እንዲያስተካክሉ ግብረመልስ የተሰጣቸው መሆኑ በመማር ማስተማሩ ጥራት ላይ የሚፈጥረው ችግር ቀላል የሚባል አይደለም።

የተዘጋጀው እቅድም በዲፓርትመንትና በም/ር/መምህራን ወይም ርእሰ መምህራን ታይቶ አስተያየት ተሰጥቶበት ወደ ስራ መግባት ላይም አብዛኞቹ የሚበረታቱ ቢሆንም አሁንም በጥቂት አመራሮች ባግባቡ አለማየት የሚታዩ ችግሮች ናቸው።

እቅዱ መዘጋጀቱና በሃላፊ መታየቱ ብቻ በቂ እይደለም የትምህርቱ ይዘትና አላማ ባግባቡ ተተንትኖ መዘጋጀቱና ተግባራዊ መደረጉ ላይ የሚታየው ሙያዊ ክፍተት ቀላል የሚባል የሚባል አይደለም የመምህራን የማስታወሻ ደብተር ዝግጅት ወቅታዊነትና ጥራት፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሒደት በንቃት መሳተፍ፣ ተማሪዎች የክፍል ስነሥርዓትን መጠበቅ፣ በመማር ማስተማር ክፍል ውስጥ የመምህራንና ተማሪዎች መስተጋብር ጤናማነት ላይ አልፎ አልፎ ችግሮች አሉ ለዚህም ችግር መነሻው ባብዛኛው ከተማሪዎች ስነምግባር ችግር የሚነሳ ቢሆንም ትምህርት ቤቱንና መምህራንን የሚመለከት አይደለም ለማለት አያስደፍርም።

የመማር ማስተማሩን ስራ ከሚያሻሽሉ ስራዎች ውስጥ የክፍ ለጊዜ ብክነት እና የአርፋጅ ተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ትልቁ ተግባር ነው በመሆኑም በየደረጃው በተደረገ ክትትል በዚህ ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም በኮቪድ፣ በህግ ማስከበር ዘመቻ ስራ እና ሌሎች ምክንያቶች የባከነው ክፍለጊዜ ከፍተኛ ነው።

ይሁንና የባከነውን ክፍለ ጊዜ ለማካካስ እና ተጨማሪ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት ችግሩን ለመፍታት የተሄደው ርቀት የሚበረታታ ነው። ሆኖም አሳማኝ ባልሆነ መንገድ የሚባክኑ ክፍለጊዜያትም ቀላል ባለመሆናቸው ልዩ ትኩረት ሊሰጠውና በቀጣዩ አመት ሊለወጥ የሚገባው አሰራር ነው።

ተማሪዎች በሰአታቸው ገብተው ባግባቡ ትምህርታቸውን ሊከታተሉ ይገባል። በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አርፋጅ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ነው። ሆኖም በ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚታየው ማርፈድ ግን ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

የትምህርት ቤት አመራሩም የሚያረፍዱ ተማሪዎችን ችግር በማጥናት አልፎ አልፎ አማራጭ መፍትሄ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ ቢሆንም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በአርፋጅ ተማሪዎች ላይ በር በመዝጋት ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲቆሙ በማድረጋቸው ተማሪዎቹ ለተጨማሪ የስነምግባር ችግር እንዲጋለጡ አድርጓል። በመሆኑም ይህ ችግር አማራጭ የመፍትሄ አቅጣጫ ተቀምጦለት ሊፈታ ይገባል። እነዚህ ከመማር ማስተማር ጋር የሚታዩ ድክመቶች አመራሩ ኢንስትራክሽናል አመራር ሚናን ካለመወጣት የሚገለፁ ናቸው።

4.1.3 ሙያዊና አስተዳደራዊ ስራዎች ክትትል ነባራዊ ሁኔታ

የሙያዊና አስተዳደራዊ ክትትልና ድጋፍ ስራዎች ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን በሱፐርቫይዘሮች ባግባቡ በመሰጠት ላይ መሆኑ ይታወቃል በመሆኑም ትምህርት ቤትን በእውቀት የሚመሩ የትምህርት ቤት አመራሮች እንዳሉን ሁሉ በተቃራኒውም አንዳንድ አመራሮች በተለያዩ መነሻዎች አስተዳደራዊና የመማር ማስተማር ስራዎችን ባግባቡ ባለመምራታቸው በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ።

ከነዚህም ሙያዊና አስተዳደራዊ ክትትልና ድጋፍ ስራዎች ውስጥ የትምህርት ቤት ዋና ር/መምህርራንና ምክትል ርእሰ መምህራን በግልጽነትና በመግባባት በጋራ በመወሰን እና በውሀደት ስራዎቻቸውን እንዲሰሩ ለማስቻል በተደረገው ጥረት አብዛኞቹ አመራሮች ተናበው፣ ትምህርት ቤትንና መማር ማስተማርን ማእከል አድርገው በመስራታቸው ሰላማዊ መማር ማስተማርን ከመፍጠራቸውም በላይ የተማሪዎችን ውጤታማነት በማሳደግ አርአያ የሆነ ስራ በመስራታቸው በወላጁና አካባቢው ህብረተሰብ ልዩ እርካታና አመኔታ የፈጠሩ ትምህርት ቤቶች ተፈጥረዋል። ሆኖም ክትትልና ድጋፉ ተከታታይ ባለመሆኑና ችግሮቹም ለሚመለከታቸው የቅርብ ሃላፊዎች የማይገለጽበት ሁኔታ በመኖሩ በተቃራኒው በ 2014 ዓ.ም በአመራር ውሀደት እና አቅም ችግር ስራዎቻቸውን ማሳካት ያልቻሉ ትምህርት ቤቶችም ነበሩ።

አንድ ትምህርት ቤት አቅም በፈቀደ ምቹ ሁኔታው የተሟላ ሊሆን ይገባል ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች የከከርሰ ምድር ውሃ እና መፀዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተሰራው ስራ በአንዳንድ ቦታዎች አበረታች ሁኔታዎችን ፈጥረዋል።

በተጨማሪም በትምህርት ቢሮና ስፖላሽ በሚባል ግብረሰናይ ድርጅት የሚሰሩት የመጠጥና የመታጠቢያ ውሃዎች የሚመሰገን ነው ሆኖም በተሰራው መሰረተ ልማት ልክ ግን የእጅ መታጠቢያና የታከመ የመጠጥ ውሃ በስታንዳርዱ መሰረት ባብዛኛው ትምህርት ቤት ጥቅም ላይ ውሏል ለማለት የሚቻል አይደለም::

ምክንያቱም በየትምህርት ቤቱ ያሉ የውሃ ጡቶች ከስታንዳርድ አንፃር ሲታይ ገና አልተሟሉም። ያሉትም በቂ ክትትልና ጥበቃ ስለማይደረግላቸው በየእለቱ በተለያየ ምክንያት እየተነቀሉ ይጠፋሉ ይህ የሚሆነው በቂ የሆነ የስነ-ምግባር ስርፀት በተቋማት አለመኖሩን የሚያሳይ ነው።

ይህ ሁኔታ የሚቀየረው በተቀየረ አስተሳሰብ በመሆኑ አስተሳሰብ ላይ ጠንክሮ የመስራቱ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የትምህርት ቤት ምድረ ግቢዎች አያያዝ ውበትና የመማሪያ ክፍሎች ንጽህና ባለው አቅም ተጠብቆ ሳቢ ማራኪና ምቹ ማድረግ ለመማር ማስተማሩ ውጤታማነት እና ለትምህርት ቤቶቹ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

በመሆኑም ያሉንን ውስን ሃብቶች ባግባቡ በማደራጀትና በመምራት ትምህርት ቤቶችን ምቹ ማድረግ ይቻላል በዚህ ረገድ ልምዶችን እር በርስ በመለዋወጥ ማሳደግ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል።

ኮቪድ 19 ወረርሺኝን ምክንያት በማድረግ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ የሚሰጡ የጤና ባለሙያዎች በጊዜያዊነት በየትምህርት ቤቱ የተመደቡ መሆናቸው ይታወቃል ሆኖም እነዚህ ባለሙያዎች ከሞላ ጎደል ስራዎችን እያከናወኑ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ መሆናቸው፣ የሚሰሩትን ስራ ባግባቡ ባለመረዳት፣ አመራሩም ትኩረት ሰጥቶ ቁጥጥር ባለማድረጉ ስራቸውን ባግባቡ እየሰሩ ናቸው ማለት ግን አይቻልም።

ትምህርት ቤቶች የከተማ ግብርና ልማት መነሻዎች መሆን ይገባቸዋል። በመሆኑም የከተማ ግብርና ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በወረደው አቅጣጫ መሰረት የተለያዩ አበረታች ተግባራት ተከናውነዋል፤ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችና ችግኞች በመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ተተክለዋል ሆኖም ይህ ስራ የአንድ ሰሞን የዘመቻ ስራ ብቻ እንደሆነ የሚያስብ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ቁጥር ቀላል አይደለም። በመሆኑም ይህ አመለካከት ተቀርፎ ቋሚ የሆነ በዘመናዊ መንገድ የሚመራ የከተማ ግብርና ስራ ሊጠናከር ይገባል።

4.1.4 በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚታዩ አዋኪ ጉዳዮች ክትትልና ድጋፍ ሁኔታ

በተማሪዎች አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ እድገት ላይ ጉዳትን የሚያስከትሉ በትምህርት ቤቶች ውስጥና አካባቢ ያሉ ማናቸዉም ከትክክለኛ አካሄድ ውጪ ያሉ ሁኔታዎች በሙሉ አዋኪ ሁኔታዎች ናቸው። በነበረን የሱፐርቪዥን ክትትል በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤቶች ውጥና ውጪ አዋኪ ጉዳዮች እየተበራከቱ መጥተዋል።

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መኖሪያ ቤቶች እና ነዋሪዎች መኖራቸው፤ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አለመኖር፣ ትምህርት ቤቶች ያከራዩዋቸው ንግድ ቤቶች መኖራቸው፤ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመንገደኞች መተላለፊያ መንገድ መኖር፣ የተበላሹ ትላልቅ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦዎች እና በቆሻሻ የተበከሉ ወንዞች በግቢው ውስጥ እና አካባቢ መኖር፤ አጥር የሌላቸው እና አጥራቸው የፈረሰ ትምህርት ቤቶች መኖር፤ የንጹህ መጠጥ ውሀና መብራት መቆራረጥ፤ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የመማሪያና የመመገቢያ የክፍል እጥረት መኖር፤

በትምህርት ቤቶች የቡድን ጸብ ምክንያት የትምህርት ቤት ንብረት ማውደም እና በተማሪዎችና መምህራን ላይ የአካል ጉዳት ማድረስ፤ አሉታዊ መጠጫ ባህሎች እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚፈጸሙባቸው ቀናት በትምህርት ቤቶች ማክበር፤ ጠለፋ፣ ሱስ አምጪ ነገሮችን መጠቀም፣ ከለር ደይ፣ ክሬዚ ደይ፣ ፓንት ደይ ወዘተ--- በአብዛኛው በግል ትምህርት ቤቶች የሚታይ መሆኑ።

በትምህር ቤቶች አጥር ላይ እና አካባቢ መደበኛ ያልሆነና ህገ ወጥ ንግድ፣ አገልግሎት የማይሰጡ ሸራ ቤቶች መኖር፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች በትምህርት ቤቶች መኖራቸው፣ ከፋብሪካና ከነዋሪዎች በሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ የተበከሉ ወንዞች ሸታ መኖር፤ በትምህርት ቤት አጠገብ ከዶሮ፣ ከከብት ማርቢያና መሸጫዎች የሚመጣ ፍሳሽና ሽታ መኖር፤ ከፋብሪካ፣ ከኮንስትራክሽን እና ድንጋይ መቁረጫ የሚወጣ ብናኝ፣

ከነዋሪዎችና ከሺዶች የሚወጣና ከፍል ድረስ የሚያውክ ጭስ፣ ከመኪና፣ ጋራዥ፣ ከተለያዩ የብረታ ብረት ብየዳ፣ ከእንጨት ስራ፣ ከፋብሪካ፣ ከሙዚቃ ቤት እና ከሌሎች አካባቢዎች የሚወጣ የድምጽ ብክለት መኖር፤ በትምህርት ቤቶች መግቢያ እና መውጫ በር አካባቢ የመኪና ማቆሚያና እጥበት ስራ መኖሩ፤

የትራፊክ ምልክቶችና የእግረኛ መሻገሪያ (ዜብራ) እና የፍጥነት መገደቢያ ያለመኖር፤ በትምህርት ቤቶች በር እና አካባቢ የታክሲ መጫኛ ማውረጃ ፌርማታ መኖር፤ በግንባታ ምክንያት ተቆፍረው ውሃ ያቆሩ ጉድጓዶች መኖር፤ ለሴት ተማሪዎች ትንኮሳ የሚያጋልጡ ጫካዎች መኖር፤ የስፖርት ማቋመሪያ (ቤቲንግ) ፣ ጆተኒ፣ ከረንቡላና ጌም ዞን መጫወቻዎች መኖራቸው፤ የቀንና የሌሊት ጭፈራ ቤት መኖር፤ ማሳጅ፣ ገስት ሐውስ፣ ፔኒስዮንና ቪሌጅ ቤቶች መኖሩ፤

የሱስ አምጭ እፆች /ጫት መሸጫና ማስቃሚያ፣ ሺሻ፣ ማስትሸ፣ ካናቢስ፣ ኮኬን እና አነቃቂ እንክብል መሸጫና መጠቀሚያ ቦታዎች መኖራቸው፤ የተለያዩ የአልኮል መጠጥ ቤቶች መኖራቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ለእነዚህ አዋኪ ጉዳዮች መስፋፋት ዋና ዋና ምክንያቶች ትምህርት ቤቶቹ ከአካባቢው ማህበረሰብና የአስተዳደር አካላት ጋር በቅንጅት ያለመስራት፤ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የስራ ፈቃድ የሚሰጡ ሴክተሮች ተቋማቱ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት አለማረጋገጥና በተሰጠው ፈቃድ መሰረት ስለመሰራቱ ክትትል አለማድረግ እና እርምት እርምጃ አለመውሰድ፤ አንዳንድ የመድሀኒት ቤቶች እና መድሀኒት መደብሮች እና ክሊኒኮች ያለሐኪም ትዕዛዝ የተለያዩ አነቃቂ እና ዕጽነት ያላቸው መዳሐኒቶቸ መሸጥ፤ ልዩ የፖለቲካ ተልዕኮ ያላቸው አካላት ተማሪዎችን እና የትምህርት ማህበረሰብን ለራሳቸው አጀንዳ ማስፈጸሚያ ማድረግ ሲሆኑ አዋኪ ጉዳዮቹ በትምህርት ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አስከትለዋል።

የተማሪዎች የስነምግባር፣ የጤና እና ስነልቡና ችግሮች ታይተዋል፤ የትምህርት ጥራትና ውጤታማነት መጓደል ምክንያት ሆኗል፤ የትምህርት ቤት ግቢና አካባቢው ለመማር ማስተማር ምቹ እንዳይሆን አድርጓል፤ የአካባቢውን ብሎም የከተማውን መልካም ገጽታ አበላሽቷል፤ ለወንጀል ድርጊት መንስኤ በመሆንና ለወንጀል መስፋፋት ምክንያት ሆኗል፤ ተማሪዎችን ለከፍተኛ ሱስ አምጭ እፆች ተጠቃሚነት ተጋልጠዋል፤ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ በማርፈድና በመቅረት ያልተገባ ቦታ እንዲውሉ አድርጓል፤ የትምህርት ብክነትን አስከትሏል፤ ለተላላፊ በሽታዎች መስፋፋት ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል፤

በአጠቃላይ ጤናማ የመማር ማስተማር አካባቢ እንዳይኖር በማድረግ በትምህርት ስራ ላይ ቀጥተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ከማስከተሉም ባሻገር ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት በመስጠት ፈንታ ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታና ሁኔታ የሚያሳልፉ፣ ከትምህርት ቤት በመቅረት መጥፎ ባህርያትን የሚላመዱ የጫት፣ አደንዛዥ ዕጽ እና አልኮል መጠጥ በመጠቀም በቡድን ወደ እርስ በርስ ግጭት የሚያመሩ ተማሪዎች እዚህም እዚያም በመከሰታቸው የሚጠበቀው ውጤት እንዳይመጣ ተጽዕኖ አሳድሯል።

እነዚህን አዋኪ ጉዳዮች ለመከላከልና ለማስወገድ ትምህርት ቢሮው እና በስሩ ያሉ የክ/ከተማ፣ የወረዳና ትምህርት ቤት መዋቅሮች ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በተናጠል እየሰሩ ቢሆንም ስራዎቹ ቀጣይነት ያላቸው ባለመሆኑ እና ችግሮቹ ውስብስብ በመሆናቸው በሚፈለገው ልክ ሊወገዱ አልቻሉም።

ስለሆነም በመማር ማስተማሩ ላይም እያሳደሩት ያለው ተጽዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና አድማሱን እያሰፋ መጥቶ የተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ከመፍጠሩም ባሻገር የማህበረሰቡም የደህንነት ስጋት ምንጭ እየሆነ እየመጣ ነው።

በአንፃሩ የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያቤቶች የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተው በተጠናከረ መልኩ በጋራ እየተከላከሉት አይደለም፤ ይሁንና ውስብስብና የማህበረሰብ ስጋት የሆነን ችግር በትምህርት ቢሮ አቅም ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ የሴክሮችን የቅንጅት ስራ የሚጠይቅ ነው።

በመሆኑም የትምህርት አዋኪ ጉዳዮችን ተከታትሎ ከስር መሰረቱ ለማስወገድ ትርጉም ያለው የሴክሮች የቅንጅት ስራን ተግባራዊ ማድረግ ስለሚያስፈልግ በጋራ ችግሮችንና ምንጫቸውን እኩል መረዳት፤ ለመፍትሄውም በጋራ መቆምና በአጭር መካከለኛና ረጂም ጊዜ ስትራቴጂ ለመፍታት ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መውሰድ የሚችልበት ስርአት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

4.1.5 አደረጃጀት የሚገኝበት ሁኔታ

የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን አደረጃጀት በቢሮ፣ በክ/ከተማ በ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት፣ በወረዳ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በ 110 ክላስተር እንዲደራጅ ተደርጎ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

በየደረጃው ያለውን ክላስተር ሱፐርቪዥን አቅም ለማጎልበት የአመለካከት፣ የክህሎት እና የግብአት እጥረቶችን ለመፍታት ተከታታይ ሥራዎች ተከናውነዋል። በሥራ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላትና መሰናክሎችን ለመቅረፍ በተዘጋጁ ዕቅዶች ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር ወደ ስራ ለመግባት የተሰራው ስራ የሚበረታታ ነበር።

የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ስራዎች አካል የሆነው የቢፒአር እና ቢኤስ ሲ ስራዎች በስታንዳርዳቸው መሰረት በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን የቢኤስ ሲ ስራዎችን በመከለስ ከአውቶሜሽን ጋር የማስተሳሰር ስራውም እንዲጠናከር ክትትል ተደርጓል።

በየደረጃው ያለ ሞርኒንግ ብሪፊንግ ቡድንን መልሶ የማደራጀት ስራ በማከናወን አደረጃጀቱ እንዲጠናከር ተደርጓል። በትምህርት ስራው በየወቅቱ የሚከሰቱ ክፍተቶችን በመለየትና ዕቅድን መሰረት ያደረገ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ ውጤታማ ስራ ለማከናወን ችሏል።

በ 11 ዱም ክ/ከተማ፣ በሁሉም ወረዳዎች፣ በቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች፣ በአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ተከታታይ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተከናውነዋል ግብረ-መልሶችም ተሰጥተዋል። ክፍተት ባለባቸው ተቋማትም የአሰራር አቅጣጫዎች እንዲስተካከሉ ድጋፍ በመደረጉ የአሰራር ተቀራራቢነት እንዲፈጠር አድርጓል።

መምህራንም የተማሪዎች የመማር ብቃትን ለማሻሻል በየክፍሉ የንባብ ኮርነር በማዘጋጀት የማንበብ፣ የመጻፍና የማስላት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች መረጃ በማደራጀት ለይቶ የመደገፍ ስራ ተሰርቶ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል።

ነገር ግን አደረጃጀቱ የሚበረታታ ስራ ቢያከናውንም በየደረጃው ያለ አደረጃጀት በአመለካከትና በክህሎት በሚፈለገው ልክ ለውጥ አምጥቷል ማለት ግን አይደለም፣ የሪፎርም ስራዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ስራዎችን እየመዘገቡ በክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎችን የመውሰድ መጠነኛ ክፍተት ታይቷል፤ በመሆኑም ከላይ እስከታች በሚደረጉ ክትትልና ድጋፎች በሚሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎችን ከመውሰድ አንፃር መንጠባጠቦች መታየታቸው ዋና ዋናዎቹ ክፍተቶች ናቸው።

4.1.6 የትምህርት ጥራት ክትትልና ድጋፍ ሁኔታ

የትምህርት ጥራትን ከማሻሻል አንፃር የተለያዩ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራሞች ተቀርጸው እየተተገበሩ ይገኛሉ። ሆኖም አሁን ባለው ሁኔታ የተማሪዎች ውጤትና ስነ-ምግባር ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱን መገንዘብ ይቻላል። ለዚህ ማሳያ ደግሞ በሀገር አቀፍ እና ከተማ አቀፍ ፈተናዎች በሚሰጡ መመዘኛዎች የሚጠበቀውን ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ወደ ሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ ነው፤ የተማሪዎች ስነ-ምግባር በሚፈለገው መጠን አለመሻሻሉ፣ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን በሚጠበቀው ልክ እያሻሻሉ አለመሆኑ እንደ ክፍተት የሚጠቀሱ ናቸው።

የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅና የተማሪዎች የመማር ብቃትና ውጤት እንዲሻሻል የትምህርት ቤት አመራሩ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ነው። በዚህም የማንበብ፤ የመጻፍና የማስላት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ተለይተው እንዲደገፉ ስልቶችን በመቀየስ ውጤት ማምጣት የጀመሩ ርዕሳነ መምህራን ቁጥር እየጨመረ ነው።

የትምህርት አመራሩ የትምህርት ባለሙያዎችን፣ መምህራንን እና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ለመማር ማስተማሩ ስራ ውጤታማነት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ፣ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉና በተማሪዎች ውጤት እና ስነምግባር ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ በተገቢው መንገድ ለመምራት ያሳየው ቁርጠኝነት አበረታች ነው።

በየደረጃው ያለው አመራር የመማር ማስተማሩን ስራ በመምራት የአመቱ ትምህርት ከሞላጎደል ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ ያደረገው ጥረት የሚበረታታ ነው።

አመራሩ ከላይ የተገለጹት ጥንካሬዎች እንዳሉት ቢታወቅም በትምህርት ዘመኑ የማይታለፉ ድክመቶችም ነበሩበት ከነዚህ ድክመቶች ዋና ዋናዎቹ የትምህርት ዘመኑን እቅድ ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግና የሚፈለገውን አስተዳደራዊና የመማር ማስተማር ውጤት ማስመዝገብ ላይ ድክመቶች ነበሩ። ምክንያቶቹም እቅድን በጥራት የማቀድ ሙያዊ እውቀትና ልምድ እንዲሁም ተናሳሽነት ማጣት፣ ትግበራ ላይ ቸልተኛ የሆነ አስተዳደራዊ አመራር መከተል፣ የሚታዩ የአሰራር ችግሮችን ከተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር ማጣት ጋር ባለመመዘን ተጠያቂነት የሰፈነበት ስርአት አለመፍጠር፤ በእለት ደራሽ ስራዎች ላይ ማተኮር፣ ስራዎችን ሃላፊነት ወስዶ ከማከናወን ይልቅ ጠባቂ መሆን፣ ችግሮችን ቀድሞ አለመተንተንና እንዳይከሰቱ ከመከላከል ይልቅ ምላሽ ሰጪ ብቻ በመሆን በሕዝብ እና በመንግስት የተሰጠውን አደራ ባግባቡ አለመወጣት የሚስተዋሉ ድክመቶች ነበሩ።

መረጃ ለአመራሩ ወሳኝ ጉዳይ ነው በመሆኑም የመረጃ ጥራት፤ ወቅታዊነት እና ተአማኒነት በከፍተኛ ደረጃ ችግር ውስጥ ያለፈ ነበር። ለዚህ ችግር መነሻው መረጃ ዝግጅት፣ ትንተናና ስርጭት ላይ ያለው እውቀትና አመለካከት ከተጠያቂነት አንፃር አናሳ ሆኖ መታየቱ ነው። ይህ ችግር እንደቀላል መታየት የለበትም ማንኛውም ስራ የሚሰራው በጠራ መረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ነገር ግን በየደረጃዉ ያለው አመራርም ለመረጃ ስራው ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት፣ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን፣ መረጃዎችን ማዛባት፣ ለምሳሌ፦ የተማሪዎች ቁጥርን ብንመለከት ከትምህርት ቤት ጀምሮ በወረዳ ክ/ከተማ እና ቢሮ ደረጃ የሚሰጠው የተማሪዎች ብዛት ለዩኒፎርም ሲሆን ሌላ፣ ለምገባ ስራ ሲፈለግ ሌላ ሆኖ ይገኛል ይህ ችግር መነሻው መረጃውን ለብልሹ አሰራር ስራ ለመጠቀም ያለመ የሚስል እየሆነ በመምጣቱ ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ኪራይ ሰብሳቢነትና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ቀደም ሲል ትምህርት ሴክተር ላይ ያለው ጠመኔ እና ወረቀት ብቻ ነው የሚል እሳቤ ነበር። ይህ ማለት ለኪራይ ሰብሳቢነት የሚያነሳሳ ነገር አለመኖሩን ሳይሆን ሴክተሩ በራሱ እምነት ማጉደልን የሚፀየፍ ዜጋ የሚያፈራ በመሆኑ የነበሩትም የትምህርት አመራሮች ለዜጋ ሃላፊነት የሚሰማቸው በመሆኑ የወደቀ እቃ እንኳን ተነስቶ ባለቤቱ እስኪመጣ ድረስ የሚቀመጥበት ስርአትን የመሰረቱ ጠንካራ የሴክተር አመራሮች የነበሩበት ስለነበር ነው።

አሁንም በዚህ ልክ ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚፀየፉ አመራሮችና መምህራን እንዲሁም ባለሙያዎች አሉን።

ነገር ግን ጥቂት ቁጥር ያላቸው አመራሮች አዝማሚያ ከዚህ እሴት እያፈነገጠ ኪራይ ሰብሳቢነትን የተለማመዱ የትምህርት አመራሮች እየታዩ ነው። ይህ ጥፋት እያደገ ከሄደ የሴክተሩ ችግር ብቻ ሆኖ የሚያበቃ ሳይሆን ወደ ቀጣዩ ትውልድ ተሸጋግሮ ኪራይ ሰብሳቢነት የሚፀየፉት ርካሽ ተግባር ሳይሆን ቀርቶ እንደ ስራ ቆጥሮ የሚያድግ ትውልድ ስለሚፈጠር ይህ ችግርም ህዝብንና ሃገርን የሚያጠፋ ሆኖ እንደሚመጣ ነጋሪ የሚያሻው ጉዳይ ባለመሆኑ ካሁኑ እርምጃ ሊወድበት ይገባል።

ሌላው እንደ ትምህርት ጥራት ድክመት የሚታየው ጉዳይ የአገልግሎት አሰጣጣችን ጉዳይ ነው። ትምህርት የአገልግሎት ዘርፍ ስራ በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጣችን ከተግባር ተኮር ወደ እርካታ ተኮር መሸጋገር አለበት። ትምህር ቤት የህዝብ ሃብት ነው አገልግሎትን ለተገልጋያችን ስንሰጥ መሰረት ልናደርጋቸው የሚገቡ መርሆችን ባግባቡ ባለመከተላችን ስራዎቻችንን ስንሰራ ዋናውን ተገልጋይ ተማሪና ወላጅ ማሳተፍ ላይ በቂ አለመሆኑ፤ በተቀመጠው የጊዜና መጠን ስታንዳርድ መሰረት አለማገልገል፣ ትምህርትን ለሴቶችእና ልዩፍላጎት ላላቸው ሁሉ በፍትሃዊነት ተደራሽ አለማድረግ፣ ለተማሪዎቻችን እና ወላጆች በትህትናና አክብሮት አለማገልገል፣ ስራዎቻችንን ሁሉ ለሚመለከተው ባለድርሻ አካል ገልጽ አለማድረግ፣ ቅሬታዎችን ባግባቡ ተቀብሎ አለመፍታት፣ ሃብት አጠቃቀማችን ብክነት ያለበት መሆኑ አገልግሎታችንን ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል።

ጥቂት የትምህርት ቤት አመራሮች የትምህርት ጥራትና የተማሪዎችን ውጤት እና የትምህርት ቤት ደረጃ ለማሻሻል፤ በኢንፔክሽን እና በሱፐርቪዥን የሚሰጣቸውን ግብረ- መልሶች ለቅሞ በመያዝና በእቅድ ዉስጥ በማካተት፣ የግብዓት የሂደት እና የውጤት ችግሮችን እየቀረፉ መሄድ ላይ ትኩረት የማይሰጡ እና ተግባራትን በተጠያቂነት መንፈስ የማያከናውኑ ሆነው ይታያሉ። ከዚህ በተጨማሪ የት/ቤት እና የተማሪዎች ውጤት አለመሻሻል ደንታ የማይሰጣቸው፣ ከፍተኛ የሆነ የብልሹ አሰራር ውስጥ የሚገቡ፣ ያለውን የትምህርት ግብዓት (ሰብአዊ እና ቁሳዊ ሀብት) በአግባቡ አጣጥመው የማይጠቀሙ ያለውንም ቁሳዊ ሃብት ለስርቆት እና ላልተገባ ዓላማ የሚያውሉ፤ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓቱን እና ሂደቱን በአግባቡ የማይከታተሉ፣ በየት/ት ተቋሞቻቸው ከፍተኛ የሆነ የከፍለ ጊዜ ብክነት ሲኖር ምንም የማይመስላቸው፣ በጋራ እና በቡድን የመስራት እና የማሰራት ችግር ብሎም የመምራት ችግር ያለባቸው፤ ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የትምህርት ስራን አስተሳስረው

ማከናወን የማይፈልጉ፤ ከመምህሩ እና ከትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ጋር በመሆን የት/ቤት ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ማስተጋባትና የመማር ማስተማር ተግባርን መሰረት ያላደረገ ግንኙነት የሚፈጥሩ እንዲሁም የትምህረት ተቋማቸውን በቸልተኝነት የሚመሩ አመራሮች ስላሉ ተከታተሎ ማረም እና የተጠያቂነት ስርዓትን መዘርጋት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

4.1.7 የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ነባራዊ ሁኔታ

ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ለማድረግ መንግስት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። ለማሳያ የመማሪያ ክፍል ማስፋፊያ፣ በቅድመ አንደኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመመገቢ አዳራሽ ግንባታዎች፣ የመማሪያ ክፍሎች ዕድሳትና ጥገና እንዲሁም የመጸዳጃ ቤቶች እና ንጹህ ውሀ አቅርቦትን በማሻሻል አስፈላጊ የትምህርት ግብአቶችን በመማሚላት ትምህርት ቤቶችን ምቹ ሳቢ እና ማራኪ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም አሁንም ማስፋፊያ አከባቢዎች ላይ ያሉ ትምህርት ተቋማት የተማሪ ክፍል ጥምርታ እና የተለያዩ ግብአቶች እጥረት መኖሩን፤ ከዚህም ባሻገር የውስጣዊ እና ውጫዊ የትምህርት አዋኪ ጉዳዮችን በማስወገድ በኩል የሚቀሩ ስራዎች አሉ።

እንዲሁም በየትምህርት ተቋማቱ ይህንን መርህ ግብር ለማሳካት ሂደቱን የጠበቀ፣ አሳታፊ የትምህርት ቤት ማሻሻል እቅድ ባለመታቀዱ በተማሪ ወላጆችና በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የባለቤትነት ስሜት መፍጠር አለመቻል፣ የመምህራንን ጥረትና ተነሳሽነትን በማገልበት ሙያዊ ብቃታቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ አለማድረግ፣ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት አቅደውና በቂ ዝግጅት አድርገው እንዲቀርቡ አለማስቻል፣ መምህራን በብቃት ማስተማር የሚያስችል አካዳሚክ እና ሙያዊ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ አለመቻሉን የተለያዩ ጊዜያት የሱፐርቪዥን ሪፖርቶች ያመላክታሉ።

4.2 የ 2014 ዓ.ም ኢንስፔክሽን ምዘና ውጤት ዝርዝር መግለጫ

የት/ቤት ደረጃ	የት/ቤት ይዞታ	የት/ቤቶች አፈፃፀም ደረጃ				ድምር
		ደረጃ 4	ደረጃ 3	ደረጃ 2	ደረጃ 1	
ቅድመ-1 ኛ	የመንግስት	-	26	71	4	101
	የግል	-	85	264	3	352
ድምር		-	111	335	7	453
የመጀ/ ደረጃ	የመንግስት	-	74	36	-	110
	የግል	-	64	166	-	230
ድምር		-	138	202	-	340
2 ኛ/ ደረጃ	የመንግስት	-	24	19	-	43
	የግል	1	37	38	1	77
ድምር		1	61	57	1	120
ኦ-ክፍል	የመንግስት	-	1	45	11	57
አማራጭ	የግል	-	-	48	23	71
ድምር		-	1	93	34	128

በሁሉም ተቋማት	የመንግስት	-	125	219	38	382
	የግል	1	186	468	4	659
ጠቅላላ ድምር		1	311	687	42	1041

የትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ትግበራ የመጨረሻ ውጤቱ የትምህርት ቤቶች ደረጃ መሻሻል እና የተማሪዎች ውጤት ማድግ ነው በመሆኑም በ 2014 ዓ.ም ኢንስፔክሽን ከተሰራላቸው 1041 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከእቅዳንን አንፃር ደረጃ 3 እና 4 የደረሱት ትምህርት ቤቶች ብዛት 312 ናቸው ይህ በፐርሰንት ሲታይ 30 ፐርሰንት ነው። በ 2014 ዓ.ም 57 ኦ ክፍል፣ 71 አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ፣ 453 ቅድመ አንደኛ፣ 340 የመጀመሪያ ደረጃ እና 120 ሁለተኛ ደረጃ በድምሮ 1041 ትምህርት ተቋማት የስታንዳርድ ኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ ሲሆን የደረጃ ፍረጃ ውጤት በጥቅሉ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተመላክቷል።

ሰንጠረዥ፡- የጥራት ደረጃ ፍረጃ (2014 ዓ.ም)

ተ.ቁ	ተቋማት	የጥራት ደረጃ ፍረጃ (2014 ዓ.ም)											
		ብቁ ያልሆኑ						ብቁ የሆኑ					
		ደረጃ-1 ደረጃውን ያላሟላ (ከ 50% በታች)			ደረጃ-2 በማሻሻል ላይ ያለ (50%-69.99%)			ደረጃ-3 ደረጃውን ያሟላ (70%-89.99%)			ደረጃ-4 ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ (90-100%)		
		የመንግስት	የግል	ድምር	የመንግስት	የግል	ድምር	የመንግስት	የግል	ድምር	የመንግስት	የግል	ድምር
1	ኦ-ክፍሎች	11	0	11	44	0	44	2	0	2	0	0	0
2	ቅድመ	4	3	7	71	26	335	26	85	111	0	0	0
3	1ኛ ደረጃ	0	0	0	36	16	202	74	64	138	0	0	0
4	2ኛደረጃ	0	1	1	19	38	57	24	37	61	0	1	1
5	የአማራጭ መ/ት/ት ጣቢያዎች	23	0	23	48	0	48	0	0	0	0	0	0
	ጠቅላላ ድምር	38	4	42	218	468	686	126	186	312	0	1	1

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ በሚታየው መረጃ መሰረት 2014 ዓ.ም ከተሰሩ 1041 የትምህርት ተቋማት መካል 42 (4.03%) ደረጃ አንድ ፣ 686 (65.89%) ደረጃ ሁለት ፣312 (29.9%) ደረጃ ሶስት ፣ 1 (0.09%) ደረጃ አራት ናቸው። ይህ ውጤት ከ2013 ዓ.ም የስታንዳርድ ኢንስፔክሽን ውጤት ጋር ሲነጻጸር ደረጃውን ያሟሉ የትምህርት ተቋማትከ 22.9% ወደ 29.9% ማለትም 7% ልዩነት በመሻሻል አሳይተዋል። ይሁንና ከአጠቃላይ ውጤት አኳያ መሻሻል ቢኖርም በትምህርት ቤት ደረጃ ስንመለከተው ግን ደረጃ 3 የነበሩ ወደ ደረጃ 2 የተመለሱ መኖራቸው በወቅቱ ስራችን የማይጠበቅ ስለሆነ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶትና ምክንያቱ ተጠንቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል።

በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ከ2013 ዓ.ም የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ደረጃቸውን ያሟሉ ትምህርት ተቋማት በመንግስት 7.84% በግል 5.84% በመሻሻል መታየቱ በትምህርት እርከኑ ላይ ጅማሬ የሆኑ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ስራዎች ውጤት እያስመዘገቡ መሆኑን ያመላክታል። ሆኖም አሁንም በመንግስትና በግል በአማካይ 75.49% ትምህርት ተቋማት ከደረጃ በታች መሆናቸው የትምህርት እርከኑ ደግሞ ህጻናት ተገቢውን እንክብካቤ የሚያገኙበት፣ አካላቸውንና አእምሮቸውን የሚያዳብሩበት፣ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት እና ለቀጣይ የትምህርት እርከኖች መሰረት የሚጥል በመሆኑ የትምህርት ባለድርሻ አካላት የኢንስፔክሽንን፣ የሱፐርቪዝን እና የክትትልና ድጋፍ ግኝቶችን በመጠቀም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የትምህርት ተቋማቱን ደረጃ በማሻሻል አግባብነቱንና ጥራን ጠብቆ እንዲከናወን ማስቻል ይኖርባቸዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተቋማት አፈፃፀም ከ2013 ዓ.ም የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ደረጃቸውን ያሟሉ ትምህርት ተቋማት በመንግስት 10.7% በመሻሻል ሲታዩ በግል 6.37% በመቀነስ ይታያል። ይህም በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ትምህርት ቢሮ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር በህላፊነት በመምራት የህዝብ አሰፋፈርን መሰረት ያደረገ የትምህርት ቤቶች ማስፋፍያ ማድረጉ፣ ለተማሪዎች የቁሳቁስ ድጋፍ መደረጉ እና በትምህርት እርከኑ የምገባ ፕሮግራም መኖሩ እና ተከታታይ የሱፐርቪዥን ድጋፍ በመሰጠቱ በትምህርት ተቋማት ደረጃ ላይ ለውጥ ማምጣት የቻለ ተግባር ቢሆንም አሁንም ቁጥሩ ጥቂት የማይባሉ ትምህርት ተቋማት ደረጃቸውን ያልጠበቁና ለተማሪዎች ምቹ ያልሆኑ ናቸው። በመሆኑም የትምህርት ባለድርሻዎች የግል ተቋማትን ያማከለ ስትራቴጂ በመንደፍ ለተቋማቱ መሻሻል መሰራት ይጠበቅባቸዋል።

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማትአፈፃፀም ከ2013 ዓ.ም የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ደረጃቸውን ያሟሉ ትምህርት ተቋማት በመንግስት 25.81%፣ በግል 15% በመሻሻል ይታያል።

በ2014 ዓ.ም ውጭ ኢንስፔክሽን ውጤት መሰረትም ኢንስፔክሽን ከተሰራላቸው 1041 ትምህርት ተቋማት 95 (70%) ተቋማት ሂደቱን የጠበቀ ጥራት ያለው እቅድ አለማቀዳቸውን ሰነዶች ያመላክታሉ። በመሆኑም በትምህርት ቤቶች ደረጃ እና የተማሪ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል።

የአጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ጥራት ስታንዳርድ አፈፃፀም ፍረጃ ትምህርት ቤቶችን ደረጃቸውን ለማሻሻል በየደረጃው ያለው የትምህርት አመራር የግብዓት፣ የሂደትና የውጤት ስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ በትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግበር አማካይነት የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀምን ከላይ አይተናል። በመሆኑም አፈፃፀማችን በውጪ ኢንስፔክሽን ሂደት ሲታዩ ተቋማቱ ያለባቸው የግብዓት፣ የሂደትና የውጤት ክፍተቶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። በዚህ አመት በተደረገ ምዘና እንደ ጥቅል ሲታይ ከአምናው የተሻለ ቢሆንም በተናጠል ትምህርት ቤቶች ሲታዩ ግን ደረጃ 3 ደርሰው የነበሩ ትምህርት ቤቶች ወደ ደረጃ 2 የወረዱ መኖራቸውን ያሳያል። ይህ ችግር በቀጥታ የሚያያዘው ከገምጋሚው ወይም ከትምህርት ቤቱ አመራርና አያያዝ ጋር እንጂ ምንም አይነት ሌላ ምክንያት ሊመጣለት አይችልም። ቢቻል ቢቻል ደረጃ 3 የነበሩ እዛው ደረጃ 3 ላይ እንዳሉ ነጥባቸውን ማሳደግ ወይም የነበሩበትን ደረጃ ማስጠበቅ እንጂ ወደ ኋላ መውረድ የማይጠበቅ ከፍተኛ ችግር ተደርጎ መወሰድ ይገባዋል።

በትምህርት ተቋማቱ አቅም ሊሳኩ ለሚችሉ ስታንዳርዶች ትኩረት ባለመስጠት እና የአፈጻጸም ክፍተትን ውጫዊ ማድረግ ተቀባይነት የለውም።

ለምሳሌ፡- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ ባለማድረግ፣ የሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ አጠናክሮ ባለመያዝ እና ልዩ ድጋፍ ባለማድረግ፣ የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዷቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ባለመከታተል፣ የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የፕሮግራሙን

አተገባበር መከታተልና እና ድጋፍ መስጠት ባለመቻሉ፣ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ኮሚቴ የመርሃ ግብሩን አፈፃፀም መከታተልና እና ድጋፍ ማድረግ ባለመቻሉ፣ የመማር ማስተማር ሂደትና የተጓዳኝ ክበባት ተግባራትን በእቅድ ባለማካተቱ፣ አፈፃፀሙን ባለመከታተሉና ድጋፍ ባለመስጠቱ፣ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን ማበረታታትና ዕውቅና መስጠት ባለመቻሉ እንዲሁም በሌሎች ባለድርሻ አካላት መተግበር ያለባቸው ተግባራት ባለመተግበራቸው አሁንም በርካታ ትምህርት ቤቶች ስታንዳርድ ማሟላት አልቻሉም።

በአጠቃላይ በትምህርት ጥራት ዘርፍ ግምገማ ጎልተው የታዩ ክፍተቶች ከላይ የተገለጹ ከፍተኛ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው፦

አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱ፣

የኦ ክፍል እና የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ራሱን የቻለ አደረጃጀት አለመኖር፣

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት አለመተግበሩ፤

በመጀመሪያና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት አመራሩና መምህራን ውጤታማ በሆነ መልኩ የሙያ ልማት መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆናቸው እና የአመራሩ የማስተባበርና የመምራት ክፍተት በዋናነት የሚጠቀሱ ክፍተቶች ናቸው።

በቀጣይ እንደ ሱፐርቪዥን በትኩረት መመልከት ያለብን የመምህራንና የትምህርት አመራር ሙያ ብቃት ምዘና ውጤት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ነው። ይህ ምዘና መምህሩንና አመራሩን ወደብቃት ደረጃ የሚያሸጋግረው በመሆኑ ለትምህርት ጥራት ማደግና ለትምህርት ቤቶች ደረጃ መሻሻል ወሳኝ ጉዳይ ነው በመሆኑም ፈቃደኛ የሆኑ በራሳቸው የሚተማመኑ ብቁመምህራንና አመራሮች ምዘናውን ወስደው የማለፊያ ውጤት በማስመዝገብ የስራ ፈቃዳቸውን ይዘዋል በተመሳሳይ የማለፊያ ውጤት ባያመጡም ደፍረው የተመዘኑ መምህራንና አመራሮች የሚበረታቱ ናቸው ቢያንስ ፍላጎቱ አላቸው። ነገር ግን ለመፈተን ፈቃደኛ ያልሆኑ በርካታ መሆናቸው በአመለካከት ምን ያህል ከትምህርት ጥራት እሳቤ የራቅን መሆናችንን በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ስለሚገባ ያለንበትን ደረጃ በጥልቀት ልናይ ስለሚገባና አስፈላጊውን ድጋፍና ምክር በመስጠት ወደ ተሻሻለ ውጤት ማድረስ ስለሚገባ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን።

4.3 የነባር መምህራን ሙያ ብቃት ምዘና ውጤቶች

ከ2005----2013 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ነባር መምህራን ሙያ ብቃት የፀደቁ ምዘና ውጤት በትምህርት ዓይነትና በጾታ											
ተ.ቁ	የትምህርት ዓይነት	≥62.5				< 62.5			ድምር		
		ወ	ሴ	ድ	%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
1	አማርኛ	135	377	512	41%	193	551	744	328	928	1256
2	አፋን ኦሮሞ	41	25	66	62%	14	26	40	55	51	106
3	እንግሊዘኛ	258	109	367	30%	373	478	851	614	606	1220
4	ሒሳብ	396	96	492	36%	505	354	859	901	450	1351
5	ፊዚክስ	192	30	222	44%	169	113	282	361	143	504
6	ኬሚስትሪ	240	83	323	52%	169	128	297	409	211	620
7	ባዮሎጂ	270	173	443	62%	134	141	275	404	314	718

ከ2005----2013 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ነባር መምህራን ሙያ ብቃት የፀሀፍ ምዘና ውጤት በትምህርት ዓይነትና በጾታ											
ተ.ቁ	የትምህርት ዓይነት	≥62.5				< 62.5			ድምር		
		ወ	ሴ	ድ	%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
8	ጂኦግራፊ	154	55	209	36%	181	188	369	335	243	578
9	ታሪክ	46	15	61	26%	97	77	174	143	92	235
10	ስነ-ዜጋ	210	255	465	60%	124	176	300	341	431	772
11	ጤስማ	184	62	246	43%	211	121	332	395	183	578
12	ልዩ ፍላጎት	15	13	28	14%	52	118	170	67	131	198
13	ሙዙቃ	8	7	15	42%	10	11	21	18	18	36
14	ስነ-ስእል	0	0	0	0%	26	13	39	26	13	39
15	ቋንቋ	32	55	87	11%	163	534	697	195	589	784
16	ተ/ሳይንስ	94	35	129	18%	271	315	586	365	350	715
17	ማ/ሳይንስ	58	80	138	17%	185	480	665	243	560	803
18	ኤስቴቲክስ	19	16	35	6%	160	336	496	205	352	557
19	ኢንቫ/ታል ሳይንስ	9	2	11	31%	7	18	25	16	20	36
	TOTAL	2361	1488	3849	35%	3044	4178	7222	5421	5685	11,106
	ፐርሰንት	61%	39%	35%		42%	58%	65%	49%	51%	100%

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተገለፀው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በትምህርት ዓይነት የቀረበው ምዘና እንደሚያመለክተው በአጠቃላይ 11,106 የመ/ደ/ት/ቤቶች ነባር መምህራን የተመዘኑ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 35% ተመዛኞች ማለፊያ ውጤቱን (62.5% እና በላይ) ማስመዝገብ የቻሉ ናቸው። አ/ኦሮሞ፤ ኬሚስትሪ፤ ባዮሎጂ እና ስነ-ዜጋ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በላይ የሚሆኑት ተመዛኞች በጹሁፍ ምዘናው ማለፊያ ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ ሲሆን። በስነ ጥበብ የትምህርት አይነት ደግሞ ማለፊያ ውጤት ማስመዝገብ የቻለ ተመዛኝ እንደሌለ ያሳያል።

4.4 የአዲስ መምህራን ሙያ ብቃት ምዘና ውጤቶች

ከ 2008 ዓ/ም---2013 ዓ/ም የሙያ ብቃት የጹሁፍ ምዘና የተመዘኑ የኮተቤ ዩኒቨርስቲ የዲፕሎማ ተመረቂ አዲስ መምህራን ውጤት በትምህርት ዓይነትና በጾታ											
ተ.ቁ	የትምህርት ዓይነት	የጹሁፍ ምዘና የተመዘኑ			ከ≥ 70%				< 70 %		
		ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	%	ወ	ሴ	ድ
1	አማርኛ	81	165	246	5	7	12	5%	76	158	234
2	እንግሊዘኛ	144	300	444	27	37	64	14%	117	263	380
3	ሒሳብ	171	147	318	8	5	13	4%	163	142	305
4	ስነ ዜጋ	70	119	189	18	34	52	28%	52	85	137
5	ጤስማ	123	56	179	0	0	0	0%	123	56	179
6	ልዩ ፍላጎት	45	85	130	1	3	4	3%	44	82	126
7	ስነ ጥበብ	126	117	243	3	1	4	2%	123	116	239
8	ሙዚቃ	118	162	280	4	0	4	1%	114	162	276
9	ተ/ሳይንስ	140	171	311	10	17	27	9%	130	154	284
10	ማ/ሳይንስ	109	122	231	9	14	23	10%	100	108	208
11	ኢንቫይሮሜንታል ሳይንስ	135	173	308	3	0	3	1%	132	173	305
ድምር		1262	1617	2879	88	118	206	7%	1174	1499	2673
		44%	56%		43%	57%	7.%		44%	56%	93%

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው አዲስ መምህራን 2879 መምህራን ከኮተቤ ዩኒቨርስቲ ከ 2008 ---2013 ዓ/ም በ 6 ዙር በአዲስ ተመርቀው ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ማለፊያ ውጤት (70% እና በላይ) ያስመዘገቡት ወይም ብቁ የሆኑት 206(7%) ሲሆኑ ይህም እንደ አጠቃላይም እንዲሁም በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነቶች ውጤቱ ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል።

4.5 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሙያ ብቃት ምዘና ውጤቶች

የሁለተኛ ደ/ት/ቤቶች የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ነባር መምህራን በተመለከተ											
ተ.ቁ	ምዘና የተካሄደበት ዓ/ም	≥62.5%				<62.5%			ድምር		
		ወ	ሴ	ድ	በ%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
1	መስከረም 2007 ዓ/ም	167	55	222	60%	109	39	148	276	94	370
2	ሚያዚያ 2010 ዓ/ም	217	57	274	61%	133	40	173	350	97	447
3	መጋቢት 2011 ዓ/ም	354	88	442	64%	169	85	254	523	173	696
4	ግንቦት 30/2013 ዓ/ም	659	103	762	59%	442	88	530	1,101	191	1,292
5	ሰኔ 25/2014 ዓ/ም	የተፈተኑ ቢኖሩም ውጤቱ አልደረሰም									
ድምር		1,397	303	1,700	61%	853	252	1,105	2,250	555	2,805

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው በአራት ዙር 2805 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነባር መምህራን የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1700 (61%) መምህራን ለማህደረ ተግባር ምዘና ማለፊያ ውጤት (62.5% እና በላይ) ያስመዘገቡ ናቸው። ሌላው በሰንጠረዡ እንደሚታየው ከተካሄዱት የአራት ዙር ምዘናዎች የተመዛቹቹ ውጤት የ2013 ዓመቱ ውጤት ከባለፉት ሶስት ምዘናዎች ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። ለዚህ ውጤት ማነስ ጥናት ያስፈልገዋል።

4.6 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አመራር የጹሁፍ ምዘና ውጤት

ዓ/ም	የት/ቤት አመራር	≧ 62.5% ውጤት				˂ 62.5% ውጤት			ድምር			
		ወ	ሴ	ድ	በ%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ምርመራ
2007	ር/መምህራን	6	0	6	26%	14	3	17	20	3	23	
	ሱፐርቫይዘር	9	1	10	83%	0	2	2	9	3	12	
2010	ር/መምህራን	21	0	21	66%	9	2	11	30	2	32	
	ሱፐርቫይዘር	3	0	3	38%	4	1	5	7	1	8	

ዓ/ም	የት/ቤት አመራር	≥ 62.5% ውጤት				˂ 62.5% ውጤት			ድምር			
		ወ	ሴ	ድ	በ%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ምርመራ
2011	ር/መምህራን	16	1	17	46%	15	5	20	31	6	37	
	ሱፐርቫይዘር	4	3	7	100%	0	0	0	4	3	7	
2013	ር/መምህራን	10	0	10	25%	26	4	30	36	4	40	
	ሱፐርቫይዘር	5	0	5	71%	1	1	2	6	1	7	
2014	ር/መምህራን	የተፈተኑ ቢኖሩም ውጤቱ አልደረሰም										
	ሱፐርቫይዘር											
ድምር		74	5	79	48%	69	18	87	143	23	166	

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው በሶስት ዙር በተካሄደው ምዘና 166 የ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አመራሮች የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስትና የግል 2 ኛ/ደ/ት/ቤቶች አመራሮች ውስጥ 28% ነው። ከተመዘኑት 166 የት/ቤት አመራር ውስጥ ለማህደረ ተግባር ምዘና ማለፊያ ውጤት (62.5% እና በላይ) ያስመዘገቡት 79 (48%) ናቸው።

3.2.5. የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አመራር የጹሁፍ ምዘና ውጤት

ዓ/ም	የት/ቤት አመራር	≥ 62.5% ውጤት				˂ 62.5% ውጤት			ድምር			
		ወ	ሴ	ድ	በ%	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ምርመራ
2008	ር/መምህራን	36	4	40	23%	102	33	135	138	37	175	
	ሱፐርቫይዘር	43	8	51	74%	14	4	18	57	12	69	
2010	ር/መምህራን	0	0	0	0%	79	10	89	79	10	89	
	ሱፐርቫይዘር	0	0	0	0%	14	6	20	14	6	20	
2011	ር/መምህራን	18	1	19	21%	56	16	72	74	17	91	
	ሱፐርቫይዘር	13	2	15	68%	6	1	7	19	3	22	
2013	ር/መምህራን	12	1	13	19%	41	15	56	53	16	69	
	ሱፐርቫይዘር	1	0	1	9%	8	2	10	9	2	11	

2014	ር/መ/ሱፐ	የተፈተኑ ቢኖሩም ውጤቱ አልደረሰም										
ድምር		123	16	139	25.5%	320	87	407	443	103	546	

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው በአራት ዙር በተካሄደው ምዘና 546 የመ/ደረጃ ት/ቤቶች አመራሮች የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስትና የግል የመ/ደ/ት/ቤቶች አመራሮች ውስጥ 29.5% ነው። ከተመዘኑት 546 የት/ቤት አመራር ውስጥ ለማህደረ ተግባር ምዘና ማለፊያ ውጤት (62.5% እና በላይ) ያስመዘገቡት 139 (25.5%) ናቸው።

ሲጠቃለል ምዘናከተጀመረ ከ 2005 ዓ/ም እስከ 2014 ዓ/ም 17,849 የመ/ደረጃ እና የ 2 ኛ ደ/ት/ቤቶች መምህራን የሙያ ብቃት የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስትና የግል ት/ቤቶች መምህራን ውስጥ (64 %) ነው። የጹሁፍ ምዘና ከተመዘኑት 17,849 መምህራን ውስጥ 5,913 (33%) በጹሁፍ ምዘናው ማለፊያ ውጤት (62.5% እና በላይ) ማስመዝገብ የቻሉ ናቸው።

እንዲሁም የጹኑፍ ምዘና ከተመዘኑት 17,849 መምህራን ውስጥ 4534 (25%) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት ማግኘት ችለዋል።

በአጠቃላይ 712 የት/ቤት አመራር የሙያ ብቃት የጹሁፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስትና የግል ት/ቤቶች አመራሮች 29.1% የጹሁፍ ምዘና ከተመዘኑት 712 የት/ቤት አመራር ውስጥ 218 (31%) በጹሁፍ ምዘናው ማለፊያ ውጤት (62.5% እና በላይ) ማስመዝገብ የቻሉ ናቸው። እንዲሁም የጹኑፍ ምዘና ከተመዘኑት 712 የት/ቤት አመራር ውስጥ ውስጥ 190 (27%) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት ችለዋል።

ይህ የሚያሳየን አጠቃላይ መምህራንም ሆነ አመራሩ ለምዘናው ፍላጎት እንዳላሳደሩ ሲሆን ከተመዘኑትም ፈቃድ ሰርተፍኬት ያላቸው ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው መሆኑ ለፕሮግራሙ ስኬት አሉታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ሊታወቅ ይገባል።

4.7 የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት ነባራዊ ሁኔታ

የአጠቃላይ ትምህርት ሱፐርቪዥን ስራ አንዱ የትምህርት አመራር ስራ ነው። ይህ ዘርፍ ከ 2011 መጨረሻ አመት በፊት ባሉት አመታት የነበረው ተደራሽነት በጣም ውስን በመሆኑ አንድ ቀንም ሱፐርቫይዘር ደርሶባቸው የማያውቁ ትምህርት ቤቶች በርካታ ነበሩ ነገር ግን አዲስ በተጠናው አደረጃጀት ከ 2011 ሐምሌ ጀምሮ ስራው በክላስተር ተዋቅሮና አስተባባሪ አመራር ኖሮት እንዲሰራ በመደረጉ ሽፋኑ በእጅጉ አድጓል፤ በአመቱ ከ 27,686 ክፍለ ጊዜ በላይ ክሊኒካል ሱፐርቪዥን መካሄድ ችሏል።

ይህ የሚያሳየን ካሉን 110 ክላስተሮች በአማካይ ከ 251 በላይ ክፍለጊዜ የሸፈነ ድጋፍ ለመምህራን መስጠት መቻሉን ነው። በተጨማሪም የትምህርት ቤትና አመራሩን ስትራቴጂክ እቅድ አፈፃፀም በመከታተል ግብረ-መልሶች ተሰጥተዋል፤ የትምህርት ቤቶች ደረጃ የሚሻሻልባቸውን መንገዶች አመላክቷል፤ የተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር የሚሻሻልባቸውን መንገዶች አሳይቷል፤ ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲፈጠር ችግሮችን ቀድሞ በመጠቆምና በመፍታት ከፍተኛ ትግል አድርገዋል፤ ጥናትና ምርምሮችን በመስራት እና በማሰራት የመማር ማስተማር ችግሮች በጥናት እንዲፈቱ መንገድ አመላክተዋል፤ ይህ ሁሉ ስራ ሲከናወን ለክላስተር ማእከል መደበኛ በጀት ስለሌለው ከግልና መንግስት ትምህርት ቤቶች በማስተባበርና በመለመን ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን በማማከር ልምድ ልውውጦች ተካሂደዋል፣ የጥያቄና መልስ ውድድሮች በክላስተር ደረጃ ተዘጋጅተዋል።

በሂደቱም የሚበረታታ ውጤት በመመዝገቡ መምህራንና አመራሮች የሚቀበሏቸውና የሚያከብሯቸው ውጤታማና አንቱ የሚባሉ ሱፐርቫይዘሮች ተፈጥረዋል። በመሆኑም በርካታ ትምህርት ቤቶችና መምህራን የሱፐርቪዥን አገልግሎት በማግኘት ላይ ናቸው።

ሆኖም የተደራሽነቱና ሽፋኑ ማደግ እና አንቱ የተባሉ ሱፐርቫይዘሮች መታየት መጀመራቸው ብቻ በቂ አይደለም ስታንዳርዱንና የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ባግባቡ ውጤታማ ስራ ከመስራት አንፃር የሚታዩ ውስንነቶች አሉ።

በአንዳንድ ሱፐርቫይዘሮች የሚስተዋለው ስራውንና አደረጃጀቱን በጥልቅ ተረድቶ ከማስፈፀም አኳያ የሚስተዋሉ የአቅም እና ተነሳሽነት ጉድለቶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም ለምሳሌ አደረጃጀቱ/ክላስተሩ በትምህርት ቤትደረጃ እንዲሆን ሲደረግ ታሳቢ የሚያደርገው በቅርበት ትምህርት ቤትንና መማር ማስተማሩን በብቃት መደገፍ እንዲቻል መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ በተለይ የ2ኛ ደረጃ ክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ማእከላቸውን ትምህርት ቤት ለማድረግ ፍላጎት የሌላቸው የተለያየ ምክንያት በመደርደር ከክፍለ ከተማ ላለመውጣት ጥረት ሲያደርጉ የሚስተዋሉ ክላስተሮች ይታያሉ።

በሌላ ወገን ደግሞ በርካታ የትምህርት ቤት አመራሮች ለሱፐርቪዥን ክላስተር ማእከል የሚሆን ቢሮ እና ግብአት በማሟላት ለስራችን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለው ተስፋ አድርገው የሚተባበሩ ሲሆኑ ጥቂት የሚባሉ የትምህርት ቤት አመራሮች ቢሮ ለመስጠትና የሚቻላቸውን ግብአት ለመደገፍ የሚያሳዩት ፍላጎት አናሳ ሆኖ የሚታይበት ሁኔታም ያጋጥማል። ይባስ ብሎም መነሻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን የነበሩበትን ቢሮ በማሸግና ሱፐርቫይዘሮችን በማባረር ጫፍ የወጣ ተግባር የፈፀሙ አመራሮችም ተስተውለዋል።

ከሱፐርቫይዘሮችም አንዳንዶቹ የመምህሩን የክፍል ውስጥ ተግባር በተገቢው አለመደገፍ፤ ጊዜውን የመማር ማስተማር ተግባር ላይ ከማዋል ይልቅ ለግል ተግባራት ቅድሚያ መስጠት፤ የሚሰጡት ድጋፍ በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት እንዲያሻሽል ከማድረግ ይልቅ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ የማተኮር፣ ችግሮችን ለይቶ ጥናትና ምርምር ያለማድረግ፣ እንዲሁም የሚደረገው ድጋፍ የመምህሩን የማስተማር አቅም በማሻሻል የተማሪዎችን የመማር ብቃት ለማሳደግ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከመስራት ይልቅ ድጋፍ የተደረገላቸውን መምህራን ብዘት ብቻ እንደ ግብ መውሰድ፣ የተጠያቂነት ስርአት እንዲሰፍን በቂ ግፊት አለማድረግ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው። በመሆኑም የትምህርት ቤት አመራሩና ሱፐርቫይዘሩ ተቀናጅቶና ተሰናስሎ የተማሪዎችን የመማር ውጤትና ስነምግባር ማሳደግ አላማ ላይ ማዕከል አድርጎ መስራት ሊሰመርበት ይገባል።

ክፍል አምስት፡-

5. የሱፐርቪዥን ዘርፍ ቁልፍ ችግሮች ትንተናና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

5.1 ቁልፍ ችግሮች ትንተና

የአስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን ግብረመልስ ወቅታዊ አለመሆንና ለሚመለከተው አካል ባግባቡ አለመድረስ፣

የትምህርት ቤት ህብረተሰብ ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር አለመወጣት፣

የጥናትና ምርምር ስራዎች አፈፃፀም ውጤታማ አለመሆን፣

የተቋሙ ዋና ዋና የአፈጻጸም ስትራቴጀዎችና አቅጣጫዎች

ተከታታይ የሆነ አስተዳደራዊ ሱፐርቪዥን / ክትትልና ድጋፍ ማከናወን፣ ግብረመልሶችን በወቅቱ መስጠት፣

የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ የትምህርት ቤቶችን ባለቤትነት ማረጋገጥ፣

የትናትና ምርምርስራዎችን በማጠናከር ውጤታማ ማድረግ፣

ክፍል ስድስት

6. የ 2015 ትምህርት ዘመን ዕቅድ ግቦች፣ ዓላማዎችና የሚከናወኑ ተግባራት

6.1 የ 2015 ትምህርት ዘመን ዕቅድ የትኩረት መስኮች፣

1፥-ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት፣

2፥- ጥራትና ተገቢነት ያለው መማር ማስተማር፣

3፥- የትምህርት ውስጣዊ ብቃት፣

4፥- የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ዘላቂ እድገት አመራርና አስተዳደር፣

6.2 የ 2015 ትምህርት ዘመን ግቦች፣ አላማዎችና የሚከናወኑ ተግባራት

የትኩረት መስክ 1፥- ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት

ግብ 1፥- ፍትሃዊ የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነትን ማሳደግ፣

ዓላማ 1.1፥- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ አሁን ካለበት 252,864 ወደ 266,559 ማድረስ፣

ዓላማ 1.2፥- በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ አሁን ካለበት 16,890 ወደ 30,583 ማድረስ፣

ዓላማ 1.3፥- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርተ ጥቅል ተሣትፎ አሁን ካለበት 116% ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.4፥- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሣትፎ አሁን ካለበት 101.35 ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.5፥- የ 1 ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ አሁን ካለበት 126.% ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.6፥- በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የ 1 ኛ ክፍል ቅበላን አሁን ካለበት 7051 ወደ 8655 ማድረስ፣

ዓላማ 1.7፥- የ 1 ኛ ክፍል ንጥር ቅበላ አሁን ካለበት 85.90 %ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.8፥- የአንደና ደረጃ ትምህርት ቅበላ አሁን ካለበት 570,184 ወደ 633,132 ማድረስ፣

ዓላማ 1.9፥- የአፋን ኦሮሞ ትምህርት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ አሁን ካለበት 34,184 ወደ 52,142 ማድረስ፣

ዓላማ 1.10፥- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎን አሁን ካለበት 121% ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.11፥- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሣትፎ አሁን ካለበት 99.8 % ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.12፥- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12 ኛ) ቅበላ አሁን ካለበት 211,325 ወደ 222,166 ማድረስ፣

ዓላማ 1.13፥- የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12 ኛ) ቅበላ አሁን ካለበት 12,769 ወደ 20,729 ማድረስ፣

ዓላማ 1.14፥- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12 ኛ) ጥቅል ተሣትፎ አሁን ካለበት 116 % ወደ 100% ማድረስ፣

ዓላማ 1.15፥- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12 ኛ) ንጥር ተሣትፎ አሁን ካለበት 85.78% ወደ 100% ማድረስ፣

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፥-

ተግባር 1፡- ቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከክፍል (ውስጥና ውጭ) ግብአቶችን ተሟልተው ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሁለት ጊዜ በክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ፣

ተግባር 2፡- ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ በተካሄደው ቅስቀሳ ውጤታማነት እና የመሰረተ ልማት ግብዓቶችን ተደራሽነት ላይ ሁለት ጊዜ የሱፐርቪዥን ክትትል እና ድጋፍ በማካሄድ ግብረ መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡- የመማር ማስተማር ስራን ለማስጀመር የሚያስችል የተሟላ ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ሁለት ጊዜ በመከታተል፣ አፈፃፀማቸውን መቆጣጠር፣ ግብረመልስ መስጠት፣

ዓላማ **1.16፡-** የከተማውን ህዝብ ብዛትና አሰፋፈር መሰረት በማድረግ በቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ተቋማትን ቁጥርን ከ **1010** ወደ **1080**፤ አንደኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ቁጥርን ከ **818** ወደ **868** እና በ **2** ኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ቁጥርን ከ **218** ወደ **236** ማሳደግ፣

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

ተግባር 1፡- ተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ሂደት እና የትምህርት ግብዓቶችን መሟላታቸውን ሁለት ጊዜ ክትትል በማድረግ ለመማር ማስተማር ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ግብ **2፡-** ልዩ ፍላጎት ላላቸው እና ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ልዩ ድጋፍ በመስጠት ተሳትፏቸውን ማሻሻል

ዓላማ **2.1፡-** የፆታ ንጽጽር ተሣትፎን በቅድመ አንደኛ ደረጃ **0.98** ወደ **1** ፣ በአንደኛ ደረጃ **1.05** ወደ **1** በመካከለኛ ደረጃ **1.25** ወደ **1** እና በሁለተኛ ደረጃ **1.3** ወደ **1** ማድረስ፣

ዓላማ **2.2፡-** በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች እና አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የሚማሩ ጐልማሶች **11260** ከነበረበት ወደ **13,819** ደርሷል። ወደ ዘላቂ ትምህርት ሽግግር ማድረስ፣

